# ሥልጣንን ከድምፅ ኮሮጆ ሳይሆን ከሁከት ማግኘት የሚመኝ ፓርቲ

## ክፍል አንድ

ኢ.ብሳ ነመራ

07-23-14

የኢ.ፌዴሪ ምርጫ ቦርድ የህዝብ የመንግስት ሥልጣን ባለቤትነት የሚረጋገጥበትን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሃዊና ተአማኒ ለማደረግ ከአራት ዓመት ቀደም ብሎ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ፓርቲዎች ለደንቡ ተገዢ የሆኑ ዘንድ ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ ሕጋዊ ሆነው የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በደንቡ ላይ እንዲወያዩ ጥሪ አቅርቦ እንደነበር ይታወሳል። በዚህ መሰረት በርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁለት ወራት ያህል የፈጀ ውይይትና ድርድር አካሂደው በደረሱበት ሥምምነት መሰረት የስነምግባር ደንቡን ማፅደቃቸውም እነዲሁ የታወሳል። በወቅቱ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን ጨምሮ ስድስት ገደማ ፓርቲዎችን አካቶ ሲንቀሳቀስ የነበረው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) ብቻ ድርድሩን ረግጦ መውጣቱም ይታወሳል።

ይህ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነምግባር ደንብ የአገሪቱ ሕግ ሆኖ እንዲፀድቅ የፓለቲካ ፓርቲዎቹ ወስነዋል። በዚህ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሆኖ በፀደቀው የምርጫ ሥነምግባር ደንቡ መሰረት ፓርቲዎች በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ሂደት ላይ የሚያጋጥማቸውን ማናቸውንም ተግዳሮቶችና አለመግባባቶች በውይይት የሚፈቱበት የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤትም አቋቁመዋል። ለሰላማዊ የፖለቲካ ትግል የቆረጡ ፓርቲዎች በሙሉ የዚህ ምክር ቤት አባል ናቸው።

ይህ የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ከዚህ ቀደም በርካታ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ግልፅነት የጎደላቸውና ያለመግባባት የተፈጠረባቸውን ጉዳዮች በውይይት እልባት እንዲያገኙ ማደረግ አስችሏል። ለዚህ አስረጂነት ከጥቂት ወራት በፊት ውጭ አገር የሚኖሩ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎችና በአገር ውስጥ ያሉ አጋፋሪዎቻቸው "የኢትዮጵያ መንግስት ድንበር ቆርሶ ለሱዳን መሬት ሰጥቷል" የሚል ወሬ በመንዛት በሕዝቡ ዘንድ ውዥንብር ፈጥረው በነበረበት ወቅት ጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጥበት የፈለጉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች

ገዢው ፓርቲ ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ጉዳዩን ለጋራ ምክር ቤቱ አቅርበው ያገኙትን ምላሽ መጥቀስ ይቻላል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ - ኢዴፓ ሰሞኑን ህዘባዊ ስብሰባ ለመጥራት ፍቀድ ከወሰደ በኋላ የስብሰባ ጥሪ ለማድረግ ሲንቀሳቀሰ በአዲስ አበባ ፖሊስ ደረሰብኝ ያለውን ክልከላ ወደጋራ ምክር ቤቱ ለመውሰድ ወስኗል። እነዚህ ዕውነታዎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ ለሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ያለውን አዎንታዊ አስተዋፅኦ ያረጋግጣሉ።

በራሳቸው ውሳኔ የስነምግባር ደንቡን ፈርመው የጋራ ምክር ቤቱ አባል ለመሆን ያልፈቀዱ ፓርቲዎች በሌላ በኩል መንግስት የሚወስዳቸውን ፓሊሲ የማስፈፀምና ህግ የማስከበር እርምጃዎች ላይ በጋራ ምክር ቤቱ አማካኝነት ከመወያየትና ማብራሪያ ከመጠየቅ ይልቅ ተገቢ ባልሆነ መነገድ በመጠምዘዝ ህዝብን ውዥንብር ውስጥ በመከተት ሰላማዊ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማወክ መራወጥ መለያቸው ለመሆን በቅቷል።

በቅርቡ ከኤርትራው ሸአቢያ ጋር በመተባበር ኢትዮጵያን ለማተራመስ የሽብር ጥቃት ያወጀው ግንቦት 7 መስራችና መሪ አንዳርጋቸው ፅጌ እንዲሁም ማዕከሉን አስመራ አድርጎ የተዘረጋው የሽብር መረበ ውስጥ ንክኪ አላቸው በሚል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ ህጋዊ ሆነው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ተከትሎ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ ተወያይቷል። የምክር ቤቱ አባላት ሽብርተኝነትን በመከላከል ዙሪያ አቋም ይዘዋል። በውይይቱ ላይ የተሳተፉ ፓርቲዎች ይህን አቋማቸውን በይፋ አሳውቀዋል።

የጋራ ምክር ቤቱ አባል የሆነው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ዋና ፀሃፊ አቶ ሳሳሁልህ ከበደ፣ ከምርጫ 97 ወዲህ የጫጫታ ፖለቲካ ዳግም እያገረሸ መሆኑን ገልፀው "እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ችግሮቹን በጠረጴዛ ዙሪያ መፍታት ይገባዋል" ሲሉ አሳስበዋል። አያይዘውም "እንደ ግንቦት 7፣ ኦነግና ኦበነግ የመሳሰሉ በመንግስት ደረጃ በሽብርተኝነት የተፈረጁ ድርጅቶችን እንደአገር ወዳድ በመቁጠር ጠበቃ ለመሆን የሚሞክሩና በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በአድናቆት የሚፅፉ ኃይሎችም ከድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል" ብለዋል።

የምክር ቤቱ አባል የሆነው የኢትዮጵያ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ሰይድ ይመር በበኩላቸው “ ንፁሃኑን ህብረተሰብ ከሽብርተኝነት ለመከላከል መንግስት እየወሰደ ያለውን እርምጃ ፓርቲዬ በአደናቆት ይመለከተዋል። በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሕዝብ በማተራመሰ ስልጣን ለመቆናጠጥ የሚሯሯጡትን መንግስት እይተከታተለ እርምጃ መውሰድ አለበት” ብለዋል።

በሌላ በኩል መንግስት ሰሞኑን በአሸባሪው አንዳርጋቸው ፅጌና በሌሎች የሽብር ወንጀል ተጠርጣሪዎች ላይ የወሰደውን እርምጃ እንደመብት ጥሰት በመቁጠር የፉከራ ቃና ያላቸው መግለጫዎች ያወጡ ፓርቲዎች አሉ። ከእነዚህ መሃከል የምርጫ ስነምግባር ደንቡ ላይ የተደረገውን ውይይት ረግጦ የወጣው አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲና የስነምግባር ደንቡ ከፀደቀ በኋላ የተመሰረተው፣ ሆኖም የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባል የመሆን መብቱን መጠቀም ያልፈቀደው ሰማያዊ ፓርቲ ያወጡት መግለጫ ተጠቃሽ ነው። በዚህ ፅሁፍ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች የስነምግባር ደንብ ለማዘጋጀት አድርገውት የነበረውን ድርድር ረግጦ የወጣው አንድነት ለዴሞክራሲና ፍትሕ ፓርቲ ያወጣውን መግለጫ ለመመልከት ወድጃለሁ።

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሠሞኑን በአሸባሪነት ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር የዋሉና “ከፍተኛ አመራሮቼ ናቸው” ያላቸው አቶ ሃብታሙ አያሌውና አቶ ዳንኤል ሽበሺን አስመልክቶ መግለጫ አውጥቷል፡፡ መግለጫው ላይ በይፋ አይጠቀስ እንጂ የአሸባሪው ግንቦት 7 መስራችና መሪ አንዳርጋቸው ፅጌ በቁጥጥር ሥር በመዋሉ ፓርቲው የተሰማው ቁጭትም በውስጠ ታዋቂነት ተንፀባርቆበታል። በአጠቃላይ ይህ የአንድነት መግለጫ ከአንድ ሕገመንግስት ባለበት ሃገር ውስጥ፣ ሕጋዊ ሆኖ ከሚንቀሳቀስ፣ በሕዝብ ይሁንታ ሥልጣን ለመረከብ ከተዘጋጀ ፓርቲ የማይጠበቅ የወሮበላ አገላለፆች የተንፀባረቀበት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ በመግለፃወ ላይ የቀረቡ ከአንድ ሕጋዊ የፖለቲካ ፓርቲ የማይጥበቁ ፀያፍ አገላለፆችን በዚህ ፅሁፍ ላይ ከማንሳት ተቆጥቤያለሁ።

የአንድነት መግለጫ “ባለፉት 23 ዓመታት ወደር የሌለው የዴሞክራሲያዊ መብት ገፈፋና የሰብዓዊ መብት ረገጣ በዜጎች ላይ ሲፈፀም ቆይቷል” ብሎ ነው የሚጀመረው። ይህ

የአንድነት መግለጫ መግቢያ የተወሰኑ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች እንደ ድግምት ከመግለጫቸው ላይ የማይጠፉ የንግግራቸው አዝማች ነው። በዚህ የፅንፈኛ ተቃዋሚዎች የንግግር አዝማች የሚጀምረው የአንድነት መግለጫ፣ "በአሁኑ ወቅት ይህ የሠብአዊ መብት ረገጣና ድፍጠጣ በእጅጉ ተባብሦ ወደመንግሥታዊ ጥቃት መቀየሩን፣ ዜጎች መንግሥት እንዳሠማራቸው በምንጠረጥራቸው የደህንነት ኃይሎች ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በጅምላ ታስረዋል፣ ተደብድበዋል በሥውር እሥር ቤት ተወርውረው ደብዛቸው እንደጠፋ ተደረጓል።" ይላል፡፡

ይህ ከዚህ ቀደም እስኪሰለቸን ስንሰማ የቆየነው ውንጀላ መሰረተ ቢስ መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ያወቀዋል፤ ገዢውን ፓርቲ የማይደግፉም ጭምር። አንድነት በመግለጫው ላይ የጠቀሰው በመንግስትና በገዢው ፓርቲ ላይ ያነጣጠረ ውንጀላ ለኢትዮጵያ ህዝብ የተነገረ አይደለም፡፡ አንድነት በመግለጫው ላይ የዘረዘረው መሰረተ ቢስ ውንጀላ ከርእዮተ አለም ልዩነት የተነሳ የኢትዮጵያ መንግስትን ገፅታ ማጠየም የሚፈልጉ በምእራባውያን ባለፀጎች የገንዘብ ድጋፍ የሚንቀሳቀሱ ሂዩማን ራይትስ ዎችና አምነስቲ ኢንተርናሽናልን የመሳሰሉ የይስሙላ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ቡድኖች ሪፖርት ማድመቂያ እንዲሆን የተነገረ ነው።

እነሂዩማን ራይትስ ዎች አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት ገፅታ ላይ የሚያጠላ ማንኛውንም ወሬ ከየትም ቢመጣ፣ እውነት ይሁን ውሸት ማረጋገጥ ሳያስፈልጋቸው ሪፖርታቸው ውስጥ ስለሚያካትቱት አንድነት ራሱ ፈጥሮ ያቀበላቸውን ወሬ እንደወረደ ተቀብለው ሲያንፀባርቁት ተአማኒነት ያገኛል የሚል ግምት አለው። ውሸት በመቀባበል ገበያ አክራሪ ምእራባውያን መንግስታትና ባለፀጎች የማይደግፏቸውን መንግስታት ገፅታ በማበላሸት ህዝባቸው ለአመፅ እንዲነሳ ውዥንብር ውስጥ የመክተት አካሄድ የተለመደ የቀለም አብዮት ሥልት መሆኑ ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በተጨባጭ በአገሩ ስላለው ናባራዊ እውነታ የሚያውቀው እውነት፣ ባለፉት ሃያ ሦስት አመታት ዜጎች ያለአንዳች ሥጋት ያመኑበትን አመለካከት ይዘው ይህን አመለካከት አመቺ ሆኖ ባገኙት መንገድ ሲገልፁ መቆየታቸውን ነው፡፡ ዜጎች ባመኑበት አመለካከት የመደራጀት መብታቸውም መከበሩን ነው፡፡ አንድነት ፓርቲ

ለሥልጣን እስከመፎካከር የዘለቀ መብት ኖሮት መቋቋምና መንቀሳቀስ፣ የፈለገውን መዘባረቅ የቻለው ባለፉ ሃያ ሦስት አመታት በተረጋገጠ የፈቀዱትን አመለካከት የመያዝና የመደራጀት ነፃነት መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቃል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ በይፋ መንግሥትን የሚተቹ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችንና መፃህፍትን ያየው ባለፉ ሃያ ሦስት አመታት ነው፡፡ አንዳንዶቹ ጋዜጦችና መፅሄቶች ህግና የሙያ ስነምግባረ ደንብንም ተላልፈው ህዝብን ለአመፅ ሲያነሳሱ፣ ሕዝብን በህዝብ ላይ ሲየነሳሱ፣ የመንግስት የስራ ሃላፊዎችን ሲዘልፉ ይስተዋዋሉ፡፡ መንግስት ይህን ሕገወጥ አካሄደ በሆደ ሰፊነት የሚያልፈው፣ የሚዲያዎቹነ ባለቤቶችና ከጀርባቸወ ያሉ ደጋፊዎቻቸውን ስለፈራ ሳይሆን፣ ሃሳብን በነጻነት የመግለፅ መብት አጠቃቀምና ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በማሰብ መሆኑንም የኢትዮጵያ ህዝብ ይረዳል።

በማንነታቸው ላይ የጭቆና ቀንበር ተጭኖባቸው የነበሩት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አሁን ይህ የጭቆናና የአፈና ቀንበር ወርዶላቸው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ሕገመንግስታዊ መብት ተረጋግጠላቸዋል። አሁን የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በቋንቃቸው የመንግስት አገልግሎት እያገኙ ነው። አሁን የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አባላት ፍርድ ቤት በጉዳያቸው ላይ የሚሟገቱት እንደድሮው በማይሰሙትና በማይናገሩት ቋንቋ አይደለም። በሚገባ ሃሳባቸውን መግለፅ በሚችሉበት የራሳቸው ቋንቋ እንጂ። የብሄራዊ ጭቆና ቀነበር ተሰባብሮ ወደቋል።

አንድነት ባለፉ ሃያ ሦስት አመታት “አለ” ብሎ እንዳወራው ሣይሆን በእነዚህ አመታት ማንም ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በቁጥጥር ሥር ውሎ አያውቅም። ማንም ያለፍርድቤት የቅጣት ውሳኔ ማረሚያ ቤት ወርዶ አያውቅም፡፡ ማንም ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ለዛውም የሪፐብሊኩ ርእሰ ብሔር ሣይፈርሙ የሞት ቅጣት ተፈጽሞበት አያውቅም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀበሌ አብዮት ጠባቂ ውሜኔ ሠዎች ተይዘው አካላቸው እስኪጎድል የተደበደቡበትን፣ በቀበሌ የአብዮት ጠባቂ ሊቀመንበር ትእዛዝ በጠራራ ፀሐይ በጥይት ተደብድበው አስከሬናቸው እንደእንስሳ ሬሣ ሜዳ ላይ ተጥሎ ይውል የነበረበት ሁኔታ ያስታውሣል፡፡ ይህ የቅርብ ጊዜ ታሪኩ ነው፡፡ በወታደራዊው ደርግ የሥልጣን ዘመን

በሚሊየን የሚቆጠሩ ዜጎች በእሥር ሲማቅቁ የነበረው፤ ተደብድበው አካላቸው እንዲጎድል የተደረገው፣ በይፋ አደባባይ ላይ በጥይት ተደብድበው የተገደሉት ያለፍርድ ቤት ትእዛዝና ውሣኔ ነበር፡፡ ያለፍርድ ቤት ውሳኔ መታሰርና መገደል ማለተይህ ነው። ባለፉ ሃያ ሶስት አመታት አንድም የዚህ አይነት ድርጊት አልተፈፀመም። የአንድነት ፓርቲ አመራሮችም ቢሆኑ ይህን ገሃድ እውነት ያውቁታል። ሆኖም ለእነሂዩማን ራይትስ ዎች ሃሰተኛ ወሬ እያቀበሉ መንግስትን ለማሳጣት ስለማይመቻቸው  እውነቱን መቀበልና በይፋ መገለፅ አይፈልጉም። የሸፍጥ ፖለቲከኞች ናቸው።

በአጠቃላይ የአንድነት ፓርቲ መግለጫ ላይ የሠፈረው ወሬ የኢፌዲሪ መንግሥትንና ገዢውን ፓርቲ የሚገልፅ አንዳችም እውነታ የለውም፡፡ ገዢው ፓርቲና የኢፌዴሪ መንግሥት አንድነት በመግለጫው ላይ ያለምንም ሃፍረት የዘረዘራቸውን ውንጀላዎች ታሪክ አድርጎ በማሥቀረት ነው የሚታወቁት፡፡ ይህን ማወቅ ልዩ ጥናት ማድረግ አይሻም፡፡ የእለት ተእለት ኑሯችን የሚመሠክረው እውነት ነው፡፡